የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎+251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251- 55 12 56 Fax +251- 55 31 55
Po.Box 17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa Ethiopia. Website:- www.aeup.org E-mail lionco.ethionet.et

ቁጥር
Ref.№ ____________
ቀን
Date ____________

# ከመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የተሰጠ የሐዘን መግለጫ

የተማረ፣ የተመራመረ፣ የሚያስብ አእምሮ፣ የሚፅፉ ጣቶች፣ የሚናገር አንደበት፣ ሀገርን፣ ህዝብን የሚያፈቅር ልብ፣ የአንድነትን፣ የባህልን፣ የኃይማኖትን፣ የነፃነትን፣ የእኩልነትን፣ የፍትህን መስፈን በእጅጉ የሚመኝ፣ ለዚያም ሌሊትና ቀን የሚያስብ፣ የሚፅፍ፣ የሚናገር፣ የሚሰራ፣ ሁለንተናዊ እውቀትን፣ ክህሎትን፣ ብቃትን፣ ችሎታን የተላበሱትን፣ የእውቀቱን ጫፍ ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌን ህልፈተ ሕይወታቸውን ዛሬ ሰኔ 4 ቀን 2013 ዓ.ም በመኢአድ ቢሮ ውስጥ ስብሰባ ላይ እያለን ልንሰማ ችለናል፡፡

እውነቱን ለመናገር ዜናውን ስንሰማ የተሰማንን ሀዘን በምን ቃላት ለመግለፅ እንደምንችል ግራ ገብቶናል፡፡ ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ በእግዚአብሔር ጥሪ መሰረት ወደማይቀረው መንገድ ተጉዘዋል፡፡ ይህ ጉዞ የሚመለሱበት ሳይሆን የሚቀርበት ነው፡፡

ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ ግን ሄደው የሚቀሩ ሳይሆን በሀገር፣ በህዝብና በትውልድ ውስጥ የነበሩ ያሉ የሚኖሩ በመሆናቸው እንኮራባቸዋለን፣ እናከብራቸዋለን፣ እንማርባቸዋለን፣ እንፅፍላቸዋለን፣ እንነግርላቸዋለን፣ እናስባቸዋለን፣ እንዘክራቸዋለን፣ እናስተምርባቸዋለን፣ ስለዚህ አብረውን ይኖራሉና እንደሄዱ አይቀሩም፡፡

ኢትዮጵያ የ1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥን ተከትሎ ኢትዮጵያን ህዝቡ የደረሰበትን የታሪክ ክህደት፣ የሰንደቅ ዓላማ ውርደት፣ የቅርስ ክስረት፣ የሕዝብ ውርደት፣ የፍትህ መዛባት፣ የእኩልነት መታጣት፣ የዘረኝነት በሽታ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲከሰት በአንደበታቸው በመምከር፣ በሰላ ብዕራቸው የተሳሳተውን የታሪክ ግድፈት ለማቃናት እውነቱን ያልሞከሩበት ሰከንድ፣ ደቂቃና ሰዓት ሌሊትና ቀናት አልነበረም፡፡ ያልተገኙበት ህዝባዊ ውይይት፣ ያላቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ የለም፡፡

መክረዋል፣ ፅፈዋል፣ ታግለዋል፣ በሀገር ውስጥ ለተመሰረተው መዐህድ /መኢአድ ጋር ሆነው ሕልፈተ ህይወታቸው እስከ ተሰማበት ድረስ እውቀታቸውን፣ ሀሳባቸውን፣ ገንዘባቸውን ያላቸውን ሁሉ ለግሰዋል፡፡ መኢአድ ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌን ሲያጣ የሚሰማው ሐዘን እጅግ ልብ የሚነካ በአመራሩ፣ በአባላቱ ዘንድ ከባድ ሐዘን ተሰምቶታል፡፡

ግን ምን ማድረግ ይቻላል ጥሪው ከላይ ነውና ምንስ እናደርጋለን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ፕ/ር ጌታቸው ኃይሌን ዳግማዊ ፕ/ር አሥራት ወ/የስ ናቸውና ሥራቸውን፣ ህልማቸውን፣ ታሪካቸውን ያስባል ይዘክራል፡፡ ለትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

ነገር ግን ዳግም አንደበታቸውን አንሰማም ሀዘኑን መሪር የሚያደርገው ይህ ነው ላለፉት ሰላሳ ዓመታት መዐህድ /መኢአድን በሁሉም መልኩ አገልግለዋል፡፡ አባላትን አስተምረዋል፣ የነፃነትን፣ የእኩልነትን፣ የፍትህን፣ የዴሞክራሲን፣ የታሪክን እውነተኛ መንገድ አሳይተዋል፡፡

ሐዘኑም ለመኢአድ ከባድ የሚያደርገው ለዚህ ነው፡፡ ነገር ግን ሥራቸው መፅናኛችን ነውና እንፅናናለን፡፡ አብረናቸውም እንኖራለን፡፡ ትውልድም በዘመን ቅብብሎሽ ይኖራቸዋል፣ ያያቸዋል፣ ይማርባቸዋል፣ ያነባቸዋል፣ ይናገራቸዋል፣ ይኮራባቸዋል፣ ይደሰትባቸዋል መኢአድም ይህ እውን እንዲሆን የሚቻላቸውን ሁሉ ይሰራል፣ ያስተባብራል፡፡

ሆኖም ግን ለፕ/ር ጌታቸው ኃይሌ የኛ አቅም የሚመጥን ባይሆንም እንኳን ከቤተሰቦቻቸው፣ ከወዳጆቻቸው፣ ከአድናቂዎቻቸው እንዲሁም ከመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሆነን ፕ/ሩን አንረሳቸውም፡፡ ሕልማቸውን እውን እናደርጋለን፡፡ አንደኛ ላዘኑት ልጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው፣ ወዳጆቻቸው ሁሉ መፅናናትን እየተመኘን፣ እግዚአብሔር አምላክ የኚህን ታላቅ አባት፣ ታላቅ ሰው ነፍሳቸውን ይማር ከደጋጎች አባቶች ዘንድም እረፍታቸውን ያደርግልን ዘንድ እንማፀናለን፡፡

“አንዲት ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!”
ሰኔ 5 ቀን 2012 ዓ.ም.
<u>አዲስ አበባ</u>

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY
AEUP